# እብደት

መቀባጠር፣

ዕቃ መስበር፣

መዘላበድ፣

መቀላመድ፣

ጨርቅ መቅደድ።

አንዱን መሳም አንዱን መንከስ፣

አንዱን መሾም አንዱን መክሰስ፣

በአጉል እምነት በዛር፣ ውቃቢ በቡዳ

ደካማው ወገን ሲጎዳ።

በጣን፣ በድኝ፣ በድቤ፣

ዳንኪራ ሲወርድ ባዶክርቤ

ከቄስ፣ከመነኩሴ ከፉቅራና ደብተራ፣

እግር ስር ጥሎ የሚያስጎራ፣

የሚያስደነግጥ የሚያስፈራ።

በመስቀል፣በመቁጠሪያ ባሽንክታብ፣

ሲቀጠቀጥ ሲደበደብ።

የመተተኛ የብልጥ ስራ፣

ክፉ ደጉን የሚያስለፈልፍ የሚያስወራ።

ያይምሮ ውጥረት የጭንቀት ምርት

የብልጦች የገቢ ምንጭ እብደት !!

የብልጣብልጥ ያባይ፣ጠንቋይ፣

የዘረፋ ተቋም፣ ሲሳይ።

ላንዱ ሰጥቶ አንዱን መንጠቅ፣

አንዱን ይዞ አንዱን መልቀቅ፣

መጨቃጨቅ

መተናነቅ፣

መጣል መውደቅ

የእብድ ፍቅር የእብድ መውደድ

ወዶ መጥላት፣ጠልቶ መውደድ

ማቀፍ፣ መሳም፣ ወይ ማሳደድ

እታች መውረድ እላይ መዝለል

ከመሬት ላይ መንከባለል።

ማቅራራት፣

ማስፈራራት፣

መዝፈን ማርገድ፣

ሙሾ ማውረድ

ከሳቁለት፣

ከሸሹለት፣

ካነገሱት፣

ካከበሩት

ዝም ካሉት፣

እንደልጅ ፊት ከሰጡት፣

ይባባሳል፣መረን ይለቃል እብደት

ማስታገሻ አደብ መግገር፣

ለበሽታው ማደንዘገር፣

ጭንቅ የሚያሶግድ፣

ሰው ባለው እንዲረካ የሚያደርግ፣

አላስፈላጊ ምኞትን የሚገታ፣

ከምቀኝነት፣ ከስግብግብነትና ከጥላቻ

ከውሸት፣ካድርባይነትና ከፍራቻ፣

እግር ብረት የሚፈታ

አላስፈላጊ ምኞትን የሚገታ።

ካልተኘ አንድ ነገር፣

ይጨምራል የብድ ቁጥር።

ሚያዝያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም.(29-05-2015)

በቅርቡ በሆላንድ በተለይም በመስተርዳም ከተማ ውስጥ በአጉል እምነት የተለከፉ ብዙ ኢትዮጵያውያን በአንድ መነኩሴ ለመፈወስ የተደረገውን ድራማ ለማስታወስ የተጻፈ ነው።

በቀን ሁለት ሽህ ኤሮ በተከራዩ የዳንስ አዳራሽ ውስጥ የተሰበሰበው ሰው ሲታይ አገር ጥሎ የወጣው አብዛኛው ያይምሮ በሽታ ያለበት ነው ለማለት ያስደፍራል።ለአገር ጉዳይ ስብሰባ ሲጠራ ብቅ የማይለው ለዚህ አጉል እምነት ነቅሎ አዳራሽ ሲሞላ ማየት ምን ያህል ደካሞች እንደሆን ያመለክታል።ለሚሰቃዩ ወገኖቻችን እርዳታ አምስት ሳንቲም ማዋጣት የማይፈልገው “ስደተኛ”ነኝ ባይ ከሚያገኘው የድጎማ ገቢ ከግማሽ በላይ የሆነውን በመድረኩ ላይ ሲሰጥ ማየት የሚያስተዛዝብ ነው።በጣም የሚገርመው ነገር ሰው እንዳያያቸው መነኩሴው ባረፉበት ቤት ጨለማ ለብሰው የሚሄዱ በመኖራቸው ሰውየው እረፍት እንዳጡ ተማረው ተናግረዋል።መነኩሴውም የዋዛ አይደሉም።አንዲ ላደረጉላት “ፈውስ”ውለታ የሁለት መቶ ኤሮ ካሜራ ገዝታ ብትሰጣቸው እንዲህ አይነት እርካሽማ ካሜራ አልቀበልም፣ከገዛሽልኝ እንደ አባ ግርማ(ሌላው እፈውሳለሁ የሚሉ መነኩሴ)እንዳላቸው ካሜራ ግዥልኝ ማለታቸው ምን ያህል ወራዳነትና ገንዘብ ሰብሳቢነት እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል። ሰው የሰጡትን አመስግኖ ይቀበላል። አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከሃምሳ ሽህ ኤሮ በላይ መሰብሰባቸው ይነገራል።የውርደታችንና የኋላ ቀርነታችን ምልክት አንዱ ይህ ድራማ ነው።ድራማው በክርስቶስ፣በአምላክና አማልክት ስም መሆኑ ደግሞ “በስሜ አጋንንት የሚያወጡ፣ድውያን የሚያነጡ ይመጣሉና እንዳትሳሳቱ የሚለውን  የአምላክ ቃል የሳተና የሚክድ ነው።ለዚህ ድራማ ከሆላንድ ብቻ ሳይሆን ከፈረንሳይ፣ከጀርመን፣ከቤልጅየም፣ከስዊዘርላንድ…ወዘተ ተጉዞ የመጣም ቁጥሩ አነስተኛ አይደለም።በመድረኩ ላይ ተፈወስኩ ያለው በወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ያው በሽታው አገርሽቶበት ሲማረር ይሰማል።በመድረኩ ላይ ዱላውን የጣለው ሽባ በሳምንቱ ወፍራም ከዘራ ጨብጦ ሲያዘግም ይታያል።አዲዮስ ገንዘብና ድካም!! የከንቱ እምነት ውጤት!!

“መነኩሴ ከገዳም አይወጣም” የሚባለው አባባል ተሽሮ ከገዳም ወጥቶ ከተማ መግባት ብቻ ሳይሆን አልኮል ከሚረጭበት፣ሴሰኝነትና ዝሙት ከሚስፋፋበት ቦታ፣፣ዲስኮ መድረክ ላይ ወጥቶ ሃሌ ሉያ እያሉ ደካማውን ማስጨፈራቸው መነኩሴውን “መንፈሳዊ” ዲጄ አድርጓቸዋል። ጭፈራ ጭፈራ ነው፤ ዳንኪራ ዳንኪራ ነው፤በሙዚቃም ሆነ በቅዳሴ ማሸብሸብ ያው ማሸብሸብ ነው።አስጨፋሪውም በዘመኑ አጠራር ያው ዲጄ ነው።በዚህ ግርግር በአመስተርዳም የሚገኘው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አባቶችን ለሁለት ከፍሏል።መነኩሴውን በማጀብ የጥቅም ተካፋይ የሆኑት ቀሳውስት ከመነኩሴው ጋር ሲሰለፉ፣ቤተመቅደሱ የእርኩሳት እምነት መድረክ አይሆንም ያሉት ቀሳውስትና ምእመናን ደግሞ በነበረው ቤተክርስቲያን ውስጥ ቀርተዋል።ባለብን የመዳከምና የመከፋፈል ችግር ላይ ይህ ሲመጣ ደግሞ ይበልጥ ይጎዳናል።የምንቃወመው ጎሰኛ መንግስትም የዚህ ተጠቃሚ ይሆናል።በደካሞች እምነትና ህመም የሚጠቀሙት ሌሎቹ ደግሞ መነኩሴውን ያስመጡት የጥቅም ተካፋይ የሆኑት ነጋዴዎች ናቸው።

በዚህ ድክመት ውስጥ ለሰጠሙት ወገኖቼ ብርታትን፣ ጥንካሬውንና መዳንን፣ከተኩላ መንጋጋም ይወጡ ዘንድ እመኝላቸዋለሁ።

mnk

አገሬ አዲስ